ኤልሳቢ አነስተኛ ፋይናንስ ተቋም

አክሲዮን ማኅበር

ELSABI

ኤልሳቢ

የመመስረቻ ፅሁፍ

ህዳር 2014

<u>አዲስ አበባ ኢትዮጵያ</u>

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

ኤልሳቤ አነስተኛ ፋይናንስ ተቋም

አክሲዮን ማኅበር

የመመስረቻ ፅሁፍ

መግለጫ

እኛ ስማችን፣ዜግነታችን እና አድራሻችን ከዚህ በታች በአንቀጽ ሁለት ላይ የተጠቀሰው ባለአክሲዮኖች በዚህ መመስረቻ ፅሁፍ አንቀጽ አንድ ላይ ስሙ የተገለጸውን አነስተኛ ፋይናንስ ተቋም በኢትዮጵያ የንግድ ህግ/አዋጅ ቁጥር 1243/2013፣በአዋጅ ቁጥር 626/2001፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚያወጣቸው ሕጎችና መመሪያዎች እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች እና በዚህ የመመስረቻ ፅሁፍ መሰረት አቋቁመናል።

Aster Gedina

አንቀጽ 1

የማኅበሩ ስም

የማህበሩ ስም "ኤልሳቢ አነስተኛ ፋይናንስ ተቋም አክሲዮን ማኅበር" (ኤልሳቢ ማይክሮ ፋይናንስ) ተብሎ ይጠራል፡፡

አንቀጽ 2

የመስራች አባላት ስም፣ ዜግነት፣ አድራሻ እና የአክሲዮን ዝርዝር

የመስራች አባላት ስም፣ ዜግነት፣ አድራሻ እና የአክሲዮን ብዛት እንደሚከተለው ነው፡፡

ተ.ቁ	የባለአክሲዮን ስም	ዜግነት	አድራሻ				የተፈረመ የአክሲዮን ብዛት	የአንዱ አክሲዮን ዋጋ	የተፈረመ ካፒታል መጠን	የተከፈለ ካፒታል መጠን
			ከተማ	ክፍለ ከተማ	ወረዳ/ ቀበሌ	የቤት ቁጥር				
1	ኤል አውቶ ኢንጂነሪንግ እና ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር	ኢትዮጵያዊ	አ.አ.	ቦሌ	07	አዲስ	50,000	1000	50,000,000	12,500,000
2	ኤልኔት ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የግ/ማህበር	ኢትዮጵያዊ	አ.አ.	ቦሌ	07	አዲስ	16,000	1000	16,000,000	4,000,000
3	ጉዲና ቱምሳ ፋውንዴሽን	ኢትዮጵያዊ	አ.አ.	ቦሌ	07	አዲስ	2000	1000	2,000,000	500,000
4	አቶ ቶኪቻ አለማየሁ ከተማ	ኢትዮጵያዊ	አ.አ.	ቦሌ	01	2132	20,000	1000	20,000,000	5,000,000
5	አቶ ናኦል ቢራቱ ሱኬሳ	ኢትዮጵያዊ	አ.አ.	ኮልፌ	13	359	1,600	1000	1,600,000	400,000
6	አቶ በቀለ አበበ ቸሬ	ኢትዮጵያዊ	አ.አ.	ለገ ጣፎ	08	1270	2,000	1000	2,000,000	500,000
7	ወ/ሮ ሌንሳ ጉዲና	አሜሪካዊ	አ.አ.	ቦሌ	01	2132	2000	1000	2,000,000	500,000

8	ወ/ሮ አስቴር ጉዲና	ጀርመናዊ	አ.አ.	ቦሌ	01	2132	2000	1000	2,000,000	500,000
9	ዶ/ር ጫልቱ አበራ የማነህ	ኢትዮጵያዊ	አ.አ.	ጉለሌ	10	2650 2932/ 2010	400	1000	400,000	100,000
10	ታክሲዬ የገንዘብ ቁጠባ እና ብድር ኃ/የተ/የኅ/ሥ/ማህበር	ኢትዮጵያዊ	አ.አ.	ቦሌ	07	አዲስ	4,000	1000	4,000,000	1,000,000

አንቀጽ 3

የማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት

የማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ ከተማ ይሆናል፡፡ ሆኖም ማህበሩ ቅርንጫፎችን በተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች ሊከፍት ይችላል፡፡

አንቀጽ 4

የማህበሩ ሥራ እና ዓላማዎች

1. የማኅበሩ ዋና ዓላማ ገንዘብ መሰብሰብና በገጠርና በከተማ ግብርና በጥቃቅንና አነስተኛ የስራ መስኮች እንዲሁም በሌሎች መሰል ስራዎች ለተሰማሩ ሰዎች ጣሪያው በብሔራዊ ባንክ የሚወሰን ብድር መስጠት ነው፡፡
2. ማኅበሩ የሚከተሉትን በሙሉ ወይም በከፊል ሊያከናውን ይችላል፡፡
   - 2.1. የውዴታም ሆነ የግዴታ ቁጠባ በተጠየቀ ጊዜ የሚከፈል እንዲሁም የጊዜ ገደብ ተቀማጭ መቀበል፣
   - 2.2. በገጠርና በከተማ ግብርና እና በሌሎች ስራዎች እንዲሁም በገጠርና በከተማ ጥቃቅንና አነስተኛ ሥራ መስኮች ለተሰማሩ ሰዎች ብድር መስጠት፣
   - 2.3. በኢትዮጵያ ውስጥ የሚከፈሉ የሃዋላ ሰነዶችን ማውጣትና መቀበል፣
   - 2.4. ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት አነስተኛ የመድን ስራ መስራት፣
   - 2.5. ዓላማቸው ገቢ ማስገኛ የሆነ እንደ ግምጃ ቤት ሰነዶችና እና ሌሎች የአጭር ጊዜ የንግድ ወረቀቶችን ብሔራዊ ባንክ በሚወስነው መሠረት መግዛት፣

2.6. ሥራውን የሚያከናዉንባቸው ህንፃዎችን ጨምሮ ማንኛውንም የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት በባለቤትነት መያዝ መንከባከብና ለሌሎች ማስተላለፍ፣

2.7. ለደንበኞች የአመራር፣ የገበያ፣ የቴክኒክና አስተዳደራዊ ምክሮች መስጠትና በእነዚህም መስኮች አገልግሎት ለማገኘት እንዲችሉ ማገዝ፣

2.8. በከተማና በገጠር በጥቃቅንና አነስተኛ ስራ መስኮች ወይም በሌሎች ምርታማ ተግባራት ላይ የተሰማሩ ሰዎች የሚያካሂዷቸውን ገቢ የሚያስገኙ ፕሮጅክቶች ማገዝ፣

2.9. ለጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ሥራዎች ወይም መሰል ምርታማ ዓላማ የሚውል ገንዘብ ማስተዳደር፣

2.10. የሀገር ውስጥ ሐዋላ አገልግሎት መስጠት፣

2.11. የፋይናንስ ኪራይ አገልግሎት በካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ሥራ አዋጅ ቁጥር 103/1990 እና ካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ሥራ(ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 807/1995 መሠረት ለተከራዮች መስጠት፣

2.12. በዲጅታል ዘዴዎች የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎት

2.13. የወኪል ባንኪንግ አገልግሎት መስጠት

2.14. ከወለድ ነፃ አነስተኛ የፋይናንስ ሥራ አገልግሎት መስጠት

2.15. ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው በሚያወጣቸው መመሪያዎች የሚወሰኑ ሌሎች ስራዎችን መስራት፣

አንቀጽ 5

የማህበሩ ካፒታል፣ የአክሲዮን ብዛት እና ዋጋ

1. ማህበሩ በጠቅላላው የተፈረመ 100,000,000 (አንድ መቶ ሚሊዮን ብር) አክሲዮን እና በካሽ የተከፈለ ብር 25,000,000 (ሃያ አምስት ሚሊዮን ብር) ያለው ሲሆን ጥሬው ገንዘብ በማህበሩ ስም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የረር ቅርንጫፍ በተከፈተ ሂሳብ ቁጥር ውስጥ ተቀምጧል፣
2. ማህበሩ እያንዳንዳቸው የ1000 (አንድ ሺህ ብር) ዋጋ ያላቸው እና አጠቃላይ የአክሲዮን ብዛት 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) የሆኑ የአክሲዮኖችን አስፍሯል፣
3. ሁሉም አክሲዮኖች ተራ አክሲዮን ሆነው በባለአክሲዮኖች ስም ኮድ ተሰጥቷቸው የተመዘገቡ ሲሆን ሁሉም አክሲዮኖች እኩል መብት እና ግዴታ አላቸው፣

አንቀጽ 6

የባለአክሲዮኖች ምዝገባ

1. ማኅበሩ የባለአክሲዮኖችን መዝገብ በዋናው መስሪያቤት መያዝ አለበት፤ መዝገቡ በወረቀት ወይም ለረጅም ዘመን በሚቆይ የኤሌክትሮኒክ ዘዴ መያዝ ይችላል፤
2. መዝገቡ የባለአክሲዮኖችን ስም፣ አድራሻ፣ ዜግነት፣ የአክሲዮኖችን ብዛትና መለያ ቁጥር፣ የተከፈለውን ገንዘብ መጠንና ባለአክሲዮኖቹ የተመዘገቡበትን ቀን መያዝ አለበት፤
3. ባለአክሲዮኖችና የሚመለከታቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች መዝገቡን በነፃ መመልከት ይችላሉ፤ ባለአክሲዮን ያልሆነ ሌላ ሰው መዝገቡን ማየት የሚችለው ለዚህ ተብሎ ማኅበሩ የወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ ሲፈጽም ነው፤
4. ማንኛውም ሰው የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ ሲፈጽም የመዝገቡን ግልባጭ ወይም በአጭር የተውጣጣ ጽሑፍ እንዲሰጠው ማኅበሩን መጠየቅ ይችላል፤ ማኅበሩ ጥያቄው በቀረበ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ግልባጩን ወይም በአጭር የተውጣጣውን ጽሑፍ ለጠያቂው መሰጠት አለበት፤
5. ጥቅም ካለው ማንኛውም ሰው ወይም ከባለአክሲዮን ጥያቄ ሲቀርብለት አግባብ ያለው የመንግስት አካል በመዝገቡ አጻጻፍ ላይ የተፈጠረ ስህተት እንዲታረም ማድረግ ይችላል፤
6. የአክሲዮን መዝገቡ ዝርዝር በትክክል ባለመጻፉ ምክንያት ለሚደርስ ማንኛውም ጉዳት የዳሬክተሮች ቦርድ አባላት በአንድነትና በተናጠል ኃላፊዎች ይሆናሉ፡፡
7. እያንዳንዱ በወረቀት የሚሰጥ የአክሲዮን ምስክር ወረቀት የሚከተሉትን ይይዛል፡
    - 7.1. የማኅበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ፊርማ፣
    - 7.2. የማኅበሩን ስም፣ ዋና መስሪያ ቤትና ማኅበሩ የሚቆይበትን ጊዜ፣
    - 7.3. የማኅበሩን ዋና ገንዘብ እና አክሲዮኑ የወጣበትን ዋጋ መጠን፣
    - 7.4. የማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ የተፈረመበትን ቀን እና ማኅበሩ በንግድ መዝገብ የተመዘገበበትን ቀንና ቦታ፣
    - 7.5. የአክሲዮኑን መለያ ቁጥር፣ መደብ፣ መደበ መደበኛ ወይም ልዩ መብት የሚሰጥ ስለመሆኑ፣ ልዩ መብት የሚሰጥ ከሆነ የመብቱን ዓይነት፣

7.6. የአክሲዮኑ ዋጋ በሙሉ ካልተከፈለ የተከፈለውን ገንዘብ መጠን ወይም ዋጋዉ በሙሉ ከተከፈለ ይህንኑ የሚያመለክት መግለጫ፣ እና

7.7. አክሲዮኑ ለውጪ ዜጋ መተላለፍ የሚችል መሆን አለመሆኑን የሚያሳይ መግለጫ፡፡

አንቀጽ 7

የባለአክሲዮን መብቶች

1. እያንዳንዱ አክሲዮን ከተጣራው ዓመታዊ ትርፍ እንዲሁም ማኅበሩ ሲፈርስ ከሚቀረው የተጣራ ንብረት ድርሻ የማግኘት መብት ይሰጣል፤
2. የትርፍ ድርሻና ማኅበሩ ሲፈርስ ከተጣራው ንብረት የሚገኘው ድርሻ ባለአክሲዮኑ ለማህበሩ ዋና ገንዘብ ገቢ ባደረገው ገንዘብ መጠን ይታሰባል፤
3. እያንዳንዱ አክሲዮን ድምፅ የመስጠት መብት ይሰጣል፤ ለባለአክሲዮኑ ድምጽ የሚሰጠው ክብደት አክሲዮኑ በማኅበሩ ዋና ገንዘብ ውስጥ የሚወክለውን መጠን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፤
4. የማኅበሩን ዋና ገንዘብ ለመጨመር በጥሬ ገንዘብ ለመሸጥ የወጡ አክሲዮኖች በሚኖሩበት ጊዜ እያንዳንዱ ባለአክሲዮን በማኅበሩ ውስጥ ባለአክሲዮኑ ባለው የአክሲዮን ድርሻ መጠን በቅድሚያ የመግዛት መብት ይኖረዋል፤
5. ማንኛውም ባለአክሲዮን ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱትንና በማኅበሩ ጽህፈት ቤት የሚገኙትን ሰነዶች በማንኛውም ጊዜ የማየት እና ቅጂዎችን የመውሰድ መብት አለው፡
    1) የማኅበሩን የሒሳብ ሚዛን፣ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ እንዲሁም የንብረት ዝርዝር መዝገብ፤
    2) ባለፉት የመጨረሻ ሦስት ተከታታይ ዓመታት በዳሬክተሮች ቦርድና በኦዲተሮች ለጠቅላላ ጉባኤዎች የቀረቡ ሪፖርቶችን፤
    3) የጉባኤዎችን ቃለ ጉባኤና በጉባኤው የተሳተፉ ባለአክሲዮኖችን መመዝገቢያ ሰነድ፤
    4) ለጉባኤ የሚቀርበውን የውሳኔ ሃሳብ፤
    5) በንግድ ሕግ አንቀጽ 311 ስር የተመለከተውን ለማኅበሩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች መዝገብ፤

6) በበጀት ዓመቱ በማኅበሩ ውስጥ ከፍተኛ ክፍያ ይከፈለው የነበረውን ሰራተኛ ስምና የተከፈለውን ጠቅላላ ክፍያ መጠን የሚያሳየውን ሰነድ፤
7) የማኅበሩን ባለአክሲዮኖች ዝርዝር የያዘውን ሰነድ፤

አንቀጽ 8

የባለአክሲዮኖች ተጠያቂነት

ማንኛውም ወሳኝ ድምጽ ያለው ባለአክሲዮን ከዚህ በታች ከተመለከቱት አንዱን ፈፅሞ ከተገኘ ተጠያቂ ይሆናል፡-

1. የማኅበሩን፣ የባለአክሲዮኖችን ወይም የማኅበሩን ገንዘብ ጠያቂዎችን ጥቅም ጉዳት ላይ የሚጥል ህገ-ወጥ ድርጊት ሆን ብሎ መፈፀም፣
2. የማኅበሩን ንብረት ከባለአክሲዮኑ ንብረት ጋር መቀላቀል፣
3. የማኅበሩን እና የባለአክሲዮኑን ማንነት አለመነጣጠል፣ ማኅበሩን ለግል ወይም ለሶስተኛ ወገን ዓላማና ጥቅም እንደ ሽፋን መጠቀም፣
4. ስለማኅበሩ የፋይናንስ አቋም የማኅበሩ ገንዘብ ጠያቂዎችን ሊያሳስት የሚችል መረጃ ሆን ብሎ ማውጣት፣
5. ከገበያ ዋጋ ባነሰ ክፍያ ወይም አግባብ ካለው የማሕበሩ አመራር ውሣኔ እና እውቅና ውጪ የማኅበሩን ሀብት ለራሱ ወይም ለሶስተኛ ወገኖች የግል ጥቅም ማዋል ወይም
6. በሕግ ከሚፈቀደው በላይ የትርፍ ክፍያ መፈፀም፡፡

አንቀጽ 9

የውክልና ሥልጣን

1. የውክልና ሥልጣን ቅጽ ይዘት፣ ውክልናው የሚቀመጥበት ቦታና ጊዜ የሚወሰነው በዳይሬክተሮች ቦርድ ነው፤ ሆኖም የጊዜ ገደቡ ስብሰባው ከሚጀመርበት ከሦስት ቀናት በፊት መጠናቀቅ አይችልም፡፡
2. በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ለመሳተፍ የሚሰጥ ውክልና በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ ወይም ሌላ አግባብነት ባለው ተቋም መረጋገጥ ግዴታ አይደለም፡፡

አንቀጽ 10

የአክሲዮን ዝውውር እና መዝገብ

1. የተፈረመ የአክሲዮን ባለቤትነት የአክሲዮን መዝገብ ጋር ተያይቶ መረጋገጥ አለበት።
2. ባለአክሲዮኖች የአክሲዮን ድርሻቸውን በሽያጭ፣ በስጦታ ወይም በችሮታ ማዘዋወር ይችላሉ።
3. የአክሲዮን ድርሻ ለሶስተኛ ወገን የሚተላለፈው የዳይሬክተሮች ቦርድ በአብላጫ ድምፅ ሲቀበል ነዉ። ይህም ሆኖ የማህበሩ ነባር ባለአክሲዮኖች ቅድሚያ የመግዛት መብት አላቸው፡፤
4. በባለአክሲዮኖች መካከል የሚደረገው የአክሲዮን ዝውውር ላይ ምንም ገደብ ሊኖርበት አይገባም። ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ አባላት የአክሲዮን ድርሻ ለመግዛት ቢፈልጉ ሽያጩ በጨረታ ይሆናል። አሁን ያሉት አባላት አክሲዮኑ ለሽያጭ ከቀረበበት ጊዜ አንስቶ እስከ ሁለት ወር ጊዜ ድረስ ካልገዙት ቅድሚያ የመግዛት መብታቸውን እንደተውት ይቆጠራል።
5. የአክሲዮን ዝውውርን አስመልክቶ የአክሲዮን ድርሻ ዋጋ የሚወሰነው በወቅቱ ባለው የገበያ ዋጋ ሲሆን ክፍያውም በአንድ ጊዜ የሚከፈል ይሆናል።
6. የሟች አባል የአክሲዮን ድርሻ ለሕጋዊ ወራሾች ይተላለፋል። ወራሾቹ የአክሲዮን ድርሻ መሸጥ ሲፈልጉ አንቀጽ 10.2 እና 10.3 ተከትሎ ይሆናል።
7. ማንኛውም የአክሲዮን ዝውውር ወይም የአክሲዮን ምደባ በጽሁፍ መደረግ ያለበት ሲሆን በዚህ አይነት ሁኔታ የዳይሬክተሮች ቦርድ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚያፀድቀው ይሆናል።

አንቀጽ 11

የማህበሩ ዓመታዊ ትርፍ ክፍያ እና ክፍፍል

1. ማኅበሩ በዓመቱ በጀት ዓመት መጨረሻ የሚያስመዘግበው ትርፍ ሲኖር ይህ ትርፍ የማህበሩ አላማ ግብ እንዲመታ እና የተቋሙን አቅም ለማጎልበት መልሶ ስራ ላይ ይውላል፤ ሆኖም በዳይሬክተሮች ቦርድ ሀሳብ አቅራቢነትና በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ የማህበሩ የተጣራ ትርፍ ለባለአክሲዮኖች እንዲከፋፈል ይደረጋል።

2. ይሁን እንጂ በጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ የተጣራ የማኅበሩ ትርፍ ለባለአክሲዮኖች እንደ ትርፍ ድርሻ ሊከፋፈል ይችላል፡፡
3. የትርፍ ክፍፍል ክፍያው በአንድ ጊዜ የሚደረግ ሲሆን ይሄውም የሚፈጸመው ግብር ከተቀነሰ በኋላ ከሕጋዊ ተቀማጭ፣ ሌሎች ተቀማጮች፣ ክፍያዎች፣ የቀድሞ ኪሳራዎች፣ ሌሎች የፀደቁ ተቀናሾች ከተደረጉ በኋላ የውጭ ኦዲተሮች ሂሳቡን ከመረመሩ በኋላ እና በመጨረሻ በጠቅላላ ጉባኤ ካጸደቀው በኋላ ይሆናል፤
4. የትርፍ ክፍፍል ቀን እና ሁኔታ በጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ውሳኔ የሚወሰን ነው።
5. ማህበሩ በዓመት አንድ ጊዜ በጀት ዓመቱ ባለቀ ባሉት ሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቱን በራሱ ድህረ ገጽ ያሳትማል፡፡

አንቀጽ 12

የማህበሩ የአስተዳደር አካላት

የማህበሩ የአስተዳደር አካላት በቅደም ተከተል ከዚህ በታች ተገልጸዋል፡-

1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ
2. የዳይሬክተሮች ቦርድ
3. የዉጭ ኦዲተሮች
4. የማህበሩ ዋና ስራአስኪያጅ

አንቀጽ 13

የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ

1. የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ የሚያደርጉት እንደነገሩ ሁኔታ የዳይሬክተሮች ቦርድ፣ የተቋቋመ እንደሆነ ኦዲተሮች፣ ሒሳብ አጣሪዎች ወይም ፍርድ ቤት ናቸው፤
2. ጠቅላላ ጉባኤው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-
   1) የማኅበሩን የሃብትና ዕዳ ሒሳብ መግለጫ፤ የትርፍና ኪሣራ ሒሳብ እንዲሁም የዳይሬክተሮች ቦርድን ሪፖርት፣ የኦዲተሮችን ሪፖርት አዳምጦ የማሻሻል ወይም የማጽደቅ፤ ወይም ያለመቀበል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በትርፍ አመዳደብና አከፋፈል

እንዲሁም በአጠቃላይ ያለፈውን የሂሳብ ዓመት ማጠቃለያ የተመለከቱ የሒሳብ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የማሳለፍ፤

2) እንደአስፈላጊነቱ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን፣ ወይም ኦዲተሮችን የመሾም ወይም የመሻር እንዲሁም የሥራ ዋጋቸውን የመወሰን፤
3) ማኅበሩ የግዴታ ወረቀቶችን እንዲያወጣ የመፍቀድ እንዲሁም ከዚሁ ጋር በተያያዘ ማኅበሩ ስለሚሰጠው መያዣ የመወሰን፤
4) በአንድ ጊዜ ወይም የመጀመርያው ሽያጭ ከተደረገበት ጊዜ አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በተለያየ መጠን ከማኅበሩ ሀብት ሀምሳ አንድ በመቶ ወይም ከዛ በላይ የሚሆነውን መጠን ማስተላለፍ የተፈለገ እንደሆነ ይህን የመፍቀድ
5) በንግድ ሕግ ለአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ በግልጽ ተለይተው ከተሰጡት ጉዳዮች በስተቀር በሌሎች የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ በሚወስንባቸው ጉዳዮች ላይ ሁሉ ውሳኔ የመስጠት፡፡
6) የማህበሩን የመመስረቻ ጸሁፍ ውስጥ ያሉትን አሰራሮች ያሻሽላሉ፤
7) የማህበሩን ዓላማዎች በዳይሬክተሮች ቦርድ ሀሳብ አቅራቢነት አግባብ ባለው ህግና በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት ያሻሽላሉ/ይቀይራሉ፤
8) የማኅበሩን ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ያፀድቃል።
9) በዚህ መመስረቻ ጽሑፍ ያልተካተቱና የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔን የሚመለከቱ ጉዳዮች አግባብ ባላቸው የንግድ ህግ ድንጋጌዎች መሠረት ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

አንቀጽ 14

የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣን

1. አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-
    1.1. የማኅበሩን መመስረቻ ጽሑፍ የማሻሻል፣
    1.2. የማኅበሩን ዋና ገንዘብ የማሳደግ ወይም የመቀነስ፣
    1.3. የማኅበሩን ዜግነት የመለወጥ፣
    1.4. ማኅበሩ እንዲፈርስ፤ ወደሌላ ዓይነት የንግድ ማኅበር እንዲለወጥ፣ እንዲከፋፈል ወይም እንዲዋሀድ የመወሰን፣

1.5. የማኅበሩን ባለአክሲዮኖች ስም፣ አድራሻ፣ ዜግነት፣ የያዙት የአክሲዮን ብዛትና የተከፈለውን የገንዘብ መጠን በተመለከተ የሚደረጉ ለውጦች የማህበሩን መመስረቻ ፅሁፍ እንደማሻሻል አይቆጠሩም፣

2. አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔው የሚጠራበት፤ አጀንዳው፤ ምልዐተ ጉባዔ እና ሌሎችም ጉዳዮች አግባብነት ባለው የንግድ ህግ ድንጋጌዎች ይመራል፡፡

አንቀጽ 15

የዳይሬክተሮች ቦርድ

1. የመጀመሪያዎቹ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በዚህ መመስረቻ ጽሑፍ መሠረት ተሹመዋል፤
2. ቀጣዮቹ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የሚሾሙት በጠቅላላ ጉባኤ ነው፤
3. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባለት የሥራ ዘመን ሶስት አመት ይሆናል ፤ ሆኖም የሥራ ዘመናቸውን ያጠናቀቁ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ለተጨማሪ የስራ ዘመናት እንደገና ሊመረጡ ይችላሉ፤
4. ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ ድምጽ የሚሰጠው ለእያንዳንዱ አባል በተናጠል ነው፡፡
5. ማህበሩ በጠቅላላ ጉባኤው ከባለአክሲዮኖች መካከል በሚመረጡ ዘጠኝ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ይመራል፤
6. የዳይሬክተሮች ህግን በመጣስ ወንጀል ሰርተዉ ከተገኙ፤ ህገወጥ ድርጊት ከፈጸሙ ወይም ስህተት ከፈጸሙ ጠቅላላ ጉባዔው ሊሽራቸው ይችላል፡፡
7. በበጀት ዓመቱ ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የቦርድ አባላት የጎደሉ እንደሆነ የቀሩት አባላት የጎደሉትን የሚተኩ አባላት መምረጥ አለባቸው፤ የተተኪዎቹ አባላት የሥራ ዘመን የሚያበቃው የጎደሉት አባላት የሥራ ዘመን በሚያበቃበት ጊዜ ነው፤
8. የተተኪ አባላት ሹመት እንዲጸድቅ ለሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባኤ መቅረብ አለበት፤ ጉባኤው ሹመቱን ሊያፀድቅ ወይም በምትካቸው ሌሎች ዳይሬክተሮችን ሊሾም ይችላል ፤ ሹመቱ በጉባኤው ባይፀድቅም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 መሠረት

የተሾሙት የቦርድ አባላት ሹመታቸው ፀንቶ በቆየበት ጊዜ የፈፀሟቸው ስራዎች ዋጋ ይኖራቸዋል፤

9. የቀሩት የቦርድ አባላት ቁጥር ከጠቅላላ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ቁጥር ከግማሽ በታች የሆነ እንደሆነ የቀሩት አባላት የጎደሉትን ለማሾም አባላቱ ከጎደሉበት ጊዜ ጀምሮ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ጠቅላላ ጉባኤውን መጥራት አለባቸዉ ፤ በጎደሉት አባላት ምትክ ሹመት እስኪደረግ ድረስ የቀሩት አባላት ማኅበሩን ያስተዳድራሉ፤

10. ሁሉም የቦርድ አባላት ስራቸዉን የተው እንደሆነ የማህበሩ ኦዲተሮች የቦርድ አባላት እንዲሾሙ ይህ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ጠቅላላ ጉባኤውን መጥራት አለባቸው፤

11. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 10 መሠረት ጠቅላላ ጉባኤው እስከሚሰበሰብ ድረስ ኦዲተሮች ማኅበሩን ያስተዳድራሉ፤ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ኦዲተሮቹ ያከናወኗቸው ሥራዎች በተለዋጭ ኦዲተሮች ወይም በሌላ ፍቃድ ባለው የኦዲት ባለሙያ መመርመር አለባቸው፡፡

12. ጠቅላላ ጉባዔው የቦርድ አባላትን በማናቸዉም ጊዜ መሻር ይችላል፤

13. ያለበቂ ምክንያት የተሻረ የቦርድ አባል ወደ ኃላፊነቱ የመመለስ መብት የለውም ፤ ሆኖም ማኅበሩን የጉዳት ካሳ መጠየቅ ይችላል፡፡

14. ማኅበሩ በዋና መስሪያቤቱ የማኅበሩ ቦርድ አባላትን፣ የስራ አስኪያጆችን፣የኦዲተሮችን፣ የማኅበሩ ፀኃፊዎችን የግል ሁኔታ፣ ሞያቸዉን፣ በሌሎች የንግድ ማኅበራት ወይም ድርጅቶች ያላቸውን ጥቅም፤ ስራ፣ የቦርድ አባልነት ወይም ሌላ ኃላፊነት ካላቸው ይህንኑ እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን የሚያሳይ መዝገብ መያዝ አለበት፤ ዳይሬክተሩ የንግድ ማኅበር የሆነ እንደሆነ የማህበሩ ስምና የዋና መስሪያቤቱን አድራሻ ማሳየት አለበት፤

15. የመጀመሪያዎቹ ዘጠኝ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እነዚህ ናቸው፤

ተ/ቁ	ሙሉ ስም	የሥራ ድርሻ
1	አቶ ቶኪቻ አለማየሁ ከተማ	ሰብሳቢ
2	አቶ ናኦል ቢራቱ ሱኬሳ	ምክትል ሰብሳቢ
3	አቶ በቀለ አበበ ቸሬ	አባል
4	ዶ/ር ጫልቱ አበራ የማነህ	አባል
5	አቶ ሁንዳኦል ፍቃዱ አብዲ	አባል
6	አቶ ጌታቸው ገለታ ወዳጆ	አባል
7	አቶ ረድኤት ፅጌብርሃን የማነህ	አባል
8	ወ/ት ፀደይ አስፋው አገኘው	አባል
9	አቶ አዲሱ በጁራ አቦዬ	አባል

አንቀጽ 16

የዳይሬክተሮች ቦርድ ስልጣን

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ በሕግ፣ በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ወይም በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች የሚሰጥ ስልጣን ይኖረዋል፤
2. የዳይሬክተሮች ቦርድ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ስልጣን እና ተግባር ይኖሩታል።

ሀ. በቋሚነት የማኅበሩን አጠቃላይ አፈጻጸም እና አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ይገመግማል።

ለ. የማህበሩን ዋና ስራአስኪያጅ ይሾማል፣ ያሰናብታል፣ ደመወዝ እና የውሎ አበል ጥቅማጥቅማቸውን ይወስናል

ሐ. የዋና ስራአስኪያጅ ስልጣኑ እና ኃላፊነቱን በማኅበሩ አላማ፣ ፖሊሲ እና መመሪያ መሠረት መወጣቱን ያረጋግጣል።

መ. አስፈላጊ የሆኑ የውሳኔ አሰጣጥ መለኪያዎችን በማስቀመጥ የማኅበሩን የስራ ፍሰት ይቆጣጠራል።

ሰ. የማህበሩ ገንዘብ አግባብነት ባለው የብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት በምን አግባብ ኢንቨስት መደረግ እንደሚገባ ጠቃሚ ነው ያለውን ምክረ ሀሳብ ለጠቅላላ ጉባዔው ያቀርባል።

ረ. የማኅበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ የቀረበለትን ረቅቅ የስራእቅድ መርምሮ ያፀድቃል፤ የተቋሙን ዋና የቢዝነስ እንቅስቃሴ ዓይነት፣ መጠንና ውጠት ይወስናል፡፡

ሠ. የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉትን የአስተዳደር ረቂቅ ሐሳቦችን ያፀድቃል፤

1. ተንቀሳቃሽ እና የማይንቀሳቀስ ንብረቶችን መግዛት፣ መሸጥ
2. ቅርንጫፍ መክፈትና ማቋቋምን ይወስናል
3. ገንዘብ መበደር፣ ማበደር፣ የራሱን ንብረት መተማመኛ ወይም ዋስትና በመስጠት፣ ወይም የሶስተኛ ወገንን ብረት በዋስትና በማስያዝ ከባንኮች እና ከአከባቢ አበዳሪዎች እነ በህግ ከተፈቀደው ዓለም አቀፍ ምንጭ ለመበደር በፍ/ቤት ወይም ከፍ/ቤት ውጪ በመወያየት በአክሲዮን ባለድርሻዎች መካከል ስላለው አለመስማማቶችን ይወስናል።

ሸ. ከባለጉዳዮች ጋር የሚኖረውን አለመግባባት በስምምነት ወይም ከፍ/ቤት ውጭ ይፈታል፡

ቀ. የማኅበሩ አመታዊ በጀት እና የስራ እቅድ ከአመራር በሚቀርበው ረቅቅ መሠረት ያፀድቃል።

በ. የአፈጻጸም ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል

ተ. ለህግ ባለሙያ እና ሌሌሎችም ባለሙያዎች የውክልና ስልጣን ይሰጣል

ቸ. የማህበሩ ባለስልጣናት የተቋሙን የባንክ አካዎንት እንዲያንቀሳቅሱ ስልጣን ይሰጣል የፊራሚዎችን ብዛት ይወስናል፡፡

ኀ. የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ዳይሬክተሮች ቦርድ የክፍያ መጠን እና የአገልግሎት ክፍያ ይወስናል፣

ነ. በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ አንቀጽ 315 ውስጥ የተጠቀሱትን ተግባራት ይፈፅማል።

አንቀጽ 17

የዳይሬክተሮች ቦርድ ኃላፊነት

ቦርዱ በሕግ፣ በማኅበሩ የመመስረቻ ጽሑፍ ወይም በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች የተሰጡትን ተግባራት የመፈፀም ግዴታ አለበት፤ ይህ ጠቅላላ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

1. የማኅበሩን ፋይናንስ የማስተዳደር፣ ማኅበሩ በቂ ዋና ገንዘብ እና ክፍያዎችን በወቅቱ የመፈጸም አቅም ያለው መሆኑን የማረጋገጥ፤
2. የማኅበሩ አስተዳደራዊ አደረጃጀት የማኅበሩን የፋይናንስ መግለጫዎችን እና ቁመናን ለመቆጣጠር የሚያስችል መሆኑን የማረጋገጥ፤
3. የማኅበሩን ለአደጋ ተጋላጭነት እና ውስጣዊ አሰራር ለመቆጣጠር የሚያስችል በቂ የአሰራር ሥርዓት የመዘርጋት፤
4. በማኅበሩ ላይ ጉዳት እንዳይደረስ መከላከል፤ መከላከል ካልተቻለም ሊደርስ የሚችለውን አሉታዊ ተጽእኖ የመቀነስ፤
5. ከላይ 1-4 የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው፤ ቦርዱ የሚከተሉት ኃላፊነቶች አሉበት፡-

ሀ. የማኅበሩ ባለአክሲዮኖች እና የቦርድ ስብሰባዎች ቃለ ጉባኤ፣ የሂሳብ መዝገብ፣ የባለአክሲዮኖች እና የዳይሬክተሮች መዛግብት እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች እንዲያዙ የማድረግ፤

ለ.የሒሳብ መዛግብት ለኦዲተሮች በአስፈላጊው ጊዜ ሁሉ እንዲቀርቡ የማድረግ፤

ሐ. የፋይናንስ እቅስቃሴን ያካተተ ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤ የማቅረብ፤

መ. በንግድ ሕግ ወይም በመመስረቻ ጽሑፉ መሠረት የማኅበሩን ጉባኤዎች የመጥራት፤

ሰ. የማኅበሩ ዋና ገንዘቡ ¾ (ሦስት አራተኛ) በኪሳራ ባጣ ጊዜ ወዲያውኑ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የመጥራት፤

ረ. በዚህ ሕግ፣ በመመስረቻ ጽሑፍ ወይም በማኅበርተኞች ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሰረት የመጠባበቂያ ገንዘብ የማቋቋም እና የመያዝ እና

ሠ. የማኅበሩ ዕዳውን የመክፈል አቅም እየቀነሰ ከሄደ ወይም እዳውን መክፈል ካቋረጠ እንደነገሩ ሁኔታ ለጥንቃቄ ዕዳን መልሶ የማዋቀር ሥነ ሥርዓት፣ እዳን መልሶ የማደራጀት ሥነ ሥርዓት ወይም የመክሠር ሥነ ሥርዓት እንዲጀመር ወይም እንዲከፈት የማድረግ፡፡

አንቀጽ 18

የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜና በቋሚነት በእየሩብ ዓመቱ በዋና ጽ/ቤት ስብሰባውን ያካሄዳል።
2. ከመደበኛ ስብሰባ ውጪ ስብሰባ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የዳይሬክተሮች ቦርድ በሰብሳቢው አማካይነት አስቸኳይ ስብሰባ ይጠራል።
3. ማንኛዉም ውሳኔ የሚተላለፈው ከዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባው ላይ ሲገኙ ወይም ሲሳተፉ ነው፤ ውሳኔዎች የሚተላለፉት በቦርዱ ስብሰባ ላይ በቀጥታም ሆነ በተወካይ በተገኙት እና በንግድ ሕግ አንቀጽ 309 መሰረት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በተሳተፉት የቦርድ አባላት የድምጽ ብልጫ ነው፤ ድምፅ እኩል ለእኩል በሚከፈልበት ጊዜ የቦርዱ ሊቀመንበር የደገፈው ሐሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል፤
4. የቦርዱ ውሳኔዎች በቃለ ጉባኤ ተይዘው በስብሰባው ላይ በአካል ወይም በተወካይበተገኙት የቦድ አባላት እና በማኅበሩ ፀሐፊ መፈረም አለባቸው፤ ቃለ ጉባኤውለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ መዝገብ ውስጥ መቀመጥ አለበት፤

አንቀጽ 19

የማህበሩ ዋና ሥራአስኪያጅ

1. የማህበሩ ዋና ስራአስኪያጅ በዳይሬክተሮች ቦርድ ይሾማል ተጠሪነቱም ለዚሁ አካል ይሆናል፡፡ በተጨማሪም የዋና ስራአስኪያጅ ደመወዝ እና ጥቅማጥቅሞች በዳይሬክተሮች ቦርድ ይወሰናል፡፡
2. የማኅበሩ ዋና ስራአስኪያጅ ቀጥሎ የተጠቀሱትን ስራዎች እና ሌሎች የማኅበሩን ዓላማ ከግብ ሊያደርሱ የሚችሉ ተግባራትን የሚያከናውኑ ይሆናል።
3. በዚሁ መሰረት ዋና ስራአስኪያጅ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ተግባራት እና ሃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

3.1. የማህበሩን ጥቅም ከግብ በሚያደርሱና በዳይሬክተሮች ቦርድ የፀደቁ ውሳኔዎችን መሠረት በማድረግ ከ3ኛ ወገን ጋር ይደራደራል፣ ውል ይፈርማል፣

3.2. የማህበሩን የእለት ተእለት ተግባራት መከታተል እና የዓመት ስራ እቅድ እና በጀት ማዘጋጀት፣ ወቅታዊ የአፈጻጸም ሪፖርት ማዘጋጀት እና ለዳይሬክተሮች ቦርድ እንዲጸድቅ ማድረግ፣ ሲፀድቅም ይሄንኑ ማስፈጸም፣

3.3. በጠቅላላ ጉባኤ እና የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ መሠረት ስራዎች እየተሰሩ ስለመሆናቸው ማረጋገጥ እና የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፣

3.4. በተፈቀደው የስራ መርሃ ግብር መሠረትና በማህበሩ የፋይናንስ ፖሊስ ወይም የሂሳብ አያያዝ ዘዴ መሠረት ወጪዎችን ማፅደቅ፣

3.5. የማህበሩን የሰው ኃይል እና የውስጥ አስተዳደር ማኑዋል፣ መመሪያና ደንብ በማዘጋጀት እንዲሁም በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅና ደንብ መሠረት የሰው ኃይል መቅጠር፣ ማስተዳደር እና ማሰናበት

3.6. ማህበሩ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚኖረው ግንኙነት ዋና ስራአስኪያጁ ሁል ጊዜም ማህበሩን ወክሎ ይገኛል።

3.7. የማኅበሩን የአፈጻጸም ሪፖርት ለዳይሬክተሮች ቦርድ እና አጋር አካላት ያቀርባል።

3.8. የማህበሩን ዋና የዓላማ ለማስፈፀም የተለያዩ ዜዴዎችን በመፍጠር ማህበሩ በችሮታ ወይም በስጦታ ሀብቶችን እንዲያገኝ ያደርጋል፣

3.9. የማህበሩን የሚንቀሳቀስ እና የማይንቀሳቀስ ንብረት ኢንዲሁም የማህበሩን ፋይናንስ ማሰራትና ማስተዳደር፣

3.10. በዋና መስሪያቤት ዋና ስራአስኪያጅ ከፋይናንስ አስተዳደር ጋር በመሆን የፋይናንስ አስተዳደር በሌለበት ቦታ ከኦፕሬሽን አስተዳደር ጋር በመሆን ወይም ለዚህ ከተመደበ ሠራተኛ ጋር በመሆን የማህበሩን ባንክ አካውንት ያንቀሳቅሳል፡፡ ሆኖም የቅርንጫፍ ባንክ አካውንት በደብዳቤ የሚከፈት ሲሆን የቅርንጫፍ ሥራአስኪያጅና አካውንታንቱ ወይም የተመደበው ሌላ ሠራተኛ የሚያንቀሳቅሱት ይሆናል፡፡

3.11. ሁሉም ቦታ ላይ ማህበሩን ይወክላል አስፈላጊ ሲሆን ግን ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡

3.12. ከዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሰጠውን ሌሎች ግዴታና ኃላፊነቶችን ያከናውናል፤

3.13. ዋና ስራአስኪያጅ በሌለበት በዳይሬክተሮች ቦርድ ለዚህ ቦታ የሚመደብ ሠራተኛ ተመሳሳይ የሆነ ሃላፊነት እና ተግባራትን ያከናውናሉ።

3.14. ዋናው ስራአስኪያጅ አግባብ ባለው ህግ፤በመመስረቻ ጽሁፍ እንዲሁም በዳይሬክተሮች ቦርድ በሚሰጡ መመሪያ መሰረት የማህበሩን የንግድ ስራ ይመራል፤

3.15. ዋናው ስራአስኪያጅ የማህበሩ አላማ ግቡን እንዲመታ ማንኛውንም ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤

3.16. ዋናው ስራአስኪያጅ በዳይሬክተሮች ቦርድ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ኃላፊነቱን እና ግዴታውን ይወጣል፤

3.17. የማኀበሩ ዋና ስራአስኪያጅ የአክሲዮን ድርሻ ዝርዝር ሁኔታን የያዘ መዝገብ እና የባለአክሲዮኖች ዝርዝር የያዘ መዝገብ በዋና ጽ/ቤት ውስጥ እንዲቀመጥ የማድረግ ሃላፊነት ይኖርበታል።

3.18. በመዝገቡ ላይ እንከን ካለ ዋና ስራ አስኪያጅ ጉድለቱን በ30 ቀናት ውስጥ የማስተካከል ሃላፊነት አለበት።

<u>አንቀጽ 20</u>

<u>የማህበሩ ኦዲተሮች</u>

1. ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የተሾሙ ኦዲተሮች ይኖሩታል፤
2. የኦዲተሮች ኃላፊነት እና ግዴታ በንግድ ሕግ ቁጥር 343-354 እና በአለም አቀፍ ፋይናንስ ሥራ አዋጅ እንዲሁም ባሉት መመሪያ ላይ በተጠቀሱት መሰረት ይሆናል፤
3. የኦዲተሮች ብዛት እና የአገልግሎት ክፍያ በጠቅላላ ጉባኤው ይወሰናል፤
4. በጠቅላላ ጉባኤው የተሾመው ኦዲተር ለሶስት አመት ያገለግላል፤

5. ኦዲተሮቹ የማኅበሩን ንብረት የሂሳብ ሚዛን የሂሳብ ዝርዝር እና ሌሎች ተያያዥ ማስረጃዎችን የመመርመር እና የማኅበሩ ንብረቶች እንዲረጋገጡ የማድረግ ስልጣን አለው።
6. ጠቅላላ ጉባዔ የውጭ ኦድተሮችን ይሾማል ያባርራል እንዲሁም ክፍያቸውንና የአገልግሎት ዘመናቸውን ይወስናል፡፡

አንቀጽ 21

በጀት ዓመት እና ሪፖርት

1. የማህበሩ የበጀት አመት እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ ጁን 30 ይሆናል፤ ሆኖም ግን የመጀመሪያው የበጀት ዓመት ማህበሩ ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ጁን 30 ይሆናል፤
2. ማህበሩ የሂሳብ አያያዙን በህግ እና በዓለም አቀፍ ሪፖርቲንግ እስታንዳርድ መሠረት መያዝ ይኖርበታል፡፡
3. ማህበሩ በዓመት ቢያንስ አንድ ጊዜ ሂሳብ መዝጋት አለበት ይህም በተፈቀደላቸው የውጭ ኦድተሮች ኦዲት ይደረጋል፡፡ ይሁን እንጂ አንድ የተፈቀደለት የውጭ ኦዲተር የማህበሩን ሂሳብ ለሦስት ተከታታይ ጊዜ ባለይ ኦድት እንዲያደርግ አይፈቀድም፡፡
4. የማህበሩ የአፈጻጸም ሪከርድ፣ የሂሳብሚዛን፣ የገቢ መግለጫን ንብረትና ወጪ የሚያሳየው የተጣራ ገቢ፣ ትርፍናኪሳራ በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30 ይዘጋጃል፡፡የሚዘጋጀውም በንግድ ህጉ አንቀጽ 426 እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መስፈርት መሰረት ሆኖ ለሚመለከተው አካል ይቀርባል፡፡

አንቀጽ 22

ማህበሩ የሚቆይበት ጊዜ

ማህበሩ ላልተወሰነ ጊዜ የተቋቋመ ነው፡፡ ሆኖም በንግድ ሕጉ አንቀጽ 473 ውስጥ በተጠሱት ሁኔታዎች/ምክንያቶች ሊፈርስ ይችላል፡፡

አንቀጽ 23

የአደራጆች የትርፍ ድርሻ

1. አደራጆች ማህበሩ እንዲቋቋም በማነሳሳታቸው፣ ካፒታል እንዲዋጣ በማድረጋቸው እና ማህበሩ ሲቋቋም ኃላፊነት በመውሰዳቸው ክፍያ ይደረግላቸዋል፣

2. የማህበሩ አደራጆች ከማኅበሩ የትርፍ ድርሻ 5% ለሦስት ተከታታይ የትርፍ ዓመታት ያገኛሉ፡፡ አደራጆች ሁሉም እኩል ድርሻ ይከፈላቸዋል፡፡

አንቀጽ 24

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

1. የዚህ መመስረቻ ጽሁፍ በአማርኛ እና እንግሊዝኛ ቅጅዎች መካከል የትርጉም ሊዩነት ቢፈጠር የአማርኛው ፅሁፍ ተቀባይነት ይኖረዋል፣
2. ይህ የመመስረቻ ጽሁፍ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ሲፀድቅ እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እንዲሁም በሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ቢሮ ከተረጋገጠ በኋላ ተግባራዊ ይሆናል፣
3. በመመስረቻ ጽሁፍ ውስጥ ያልተካተቱ ሁኔታዎች በሚያጋጥሙበት ጊዜ በአነስተኛ የፋይናንስ ስራ አዋጅ ቁ.626/2001 እና በተሻሻለው አዋጅ ቁ. 1164/2012 መሠረት የሚስተናገድ ይሆናል።

አንቀጽ 25

ፊርማ

ይህ የመመስረቻ ጽሑፍ ዛሬ መስከረም ...... ቀን 2014 ዓ.ም በዚህ በአዲስ አበባ ከተማ ለባለአክሲዮኖች ቀርቦ ተነብቦ የተፈፀመና የፀደቀ ስለመሆኑ ስማችን ከላይ የተዘረዘረው ባለአክሲዮኖች በፊርማችን አረጋግጠናል፡፡

	የባለአክሲዮኖች ስም	ፊርማ	ቀን
1	ኤል አውቶ ኢንጂነሪንግ እና ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር (ህጋዊ ተወካይ ሙሉ ስም) ..ረድኤት ፅጌብርሀን የማነህ		
2	ኤልኔት ቴክኖሎጂ ኃ/የተ/የግ/ማህበር (ህጋዊ ተወካይ ሙሉ ስም).....ጸደይ አስፋው አገኘው		
3	ጉዲና ቱምሳ ፋውንዴሽን (ህጋዊ ተወካይ ሙሉ ስም)...ሌንሳ ጉዲና		
4	አቶ ቶኪቻ አለማየሁ ከተማ		
5	አቶ ናኦል ቢራቱ ሱኬሳ		
6	አቶ በቀለ አበበ ቸሬ		
7	ወ/ሮ ሌንሳ ጉዲና		
8	ወ/ሮ አስቴር ጉዲና	Aster Gudina	
9	ዶ/ር ጫልቱ አበራ የማነህ		
10	ታክሲዬ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃ/የተ/የኅ/ሥ/ማህበር (ህጋዊ ተወካይ ሙሉ ስም) ...በቀለ አበበ ቸሬ		

ዛሬ ህዳር .... ቀን 2014 ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ ተፈረመ

የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት
ቅ/12 ጽ/ቤት አ/አ
ፊርማው በጽ/ቤቱ ቀርበው ፈርመዋል፡፡
ቁጥር 14/...

አምባሳደር ተፈሪ ደምሴ
የሰነድ ማረጋገጥና
መመዝገብ ባለሙያ IV

የሰነዶች ... (ቅርንጫ...
Documents Authe...
Registration Service Bran...

የሰነዶች ማረጋገጫና
ምዝገባ አገልግሎት
አዲስ አበባ (የቅርንጫፍ አስራ ሁለት ጽ/ቤት)

የቴምብር ቀረጥ ማረጋገጫ ማህተም

የተከፈለበት ምክንያት 2000
ገንዘብ ልክ ብር
ፊደል ________ የሆነ ቴምብር ተከፍሏል ::
በቁም ብር
ደረሰኝ ቁጥር 32709158
25 09 ቀን 20 14 ዓ.ም.
የቴምብር ቀረጥ መብት አስፈፃሚ
ስም
ፊርማ